# ነጋሪት ጐሳሚው የመድረክ አመራር ምርጫ

ቆርኔሊዮስ ከአአዩ abaydagi@ yahoo.com

ጋዜጦች ስለ ‹‹መድረክ›› ሕልውና ዘላቂነት የተለያየ አስተያየት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ አንዳንዶች ‹‹የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ›› በሚል መጠሪያ ይህ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ግለሰቦች ጥምረት የተፈጠረው አንድ የጋራ ጠላት በመፍጠር ላይ አልሞ እንጂ በአማራጭነት የቀረበና ሁሉንም የጥምረቱን አባላት በጋራ የሚያግባባ የጠራ የፖለቲካ መርሃ ግብር እንዳለው እንደ አንድ የተደራጀ የፖለቲካ ኃይሎች ስብስብ በዘላቂነት ሊያቆየው የሚችል ደም (ሕይወት) ይዞ እንዳልሆነ ይተቻሉ፡፡ በዚህም ካሁን በፊት ጥምረት ለመፍጠር በተደረጉ ተመሣሣይ ጥረቶች የተስተዋሉ ድክመቶች በመንፀባረቃቸውና ለጥምረቱ መፈረካከስ አይቀሬ እንደሚሆኑ ይነገራል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት የስምንት ፓርቲዎችንና የሁለት ግለሰቦችን የተለያየ ፍላጐት አቻችሎ ማስተናገድ አስቸጋሪ የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡

እኔን የሚያሳስበኝ ግን ገና አጥንት፣ ጅማትና ሥጋ መሆን አቅቶት ተደጋግፎ እንዲቆም የተደረገው (በሙጫ የተጣበቀ ) አጽሙ ሕልውና ጉዳይ አይደለም፡፡ የውስጥ ችግራቸውን በውጭ ላይ ማሳበብ የሚቀናቸው ለዘብተኞች የዘወትር ጩኸታቸውን እንደተለመደው  በማሰማት ላይ ሲሰማሩ በቅንጅቱ ሥር የተጠለሉ ጽንፈኞች ሁሌ የሚመኙትን አመጽና ሁከት ለመቀስቀስ መድረኩን ሊጠቀሙበት አይችሉም ወይ የሚለው ነው፡፡

እርግጥ ጥምረቱ አጠቃላይ የፖለቲካ ቅኝት ምን እንደሚመስል አመላካች የሆኑ ፍንጮች በቃልም ይሁን በተግባር እያረጋገጡት ያለው እውነታ ስብስቡ ለሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ዝግጁ አለመሆኑን ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአመራር አባላቱ በሚዲያዎች የሚያስተጋቡዋቸው መልእክቶች  ይዘት ተመሣሣይ መሆን፣ በደምሳሳው

ሲታዩም በቀጣዩ ምርጫ እንደ ፓርቲ በምርጫ ተወዳድረን እናሸንፋለን የሚል እምነት እንደሌላቸውና ይልቁንም በልዩ ልዩ መንገድ መንግሥትን አስገድዶ ሥልጣን ወደመጋራት እንደሚያመሩ መጠቆማቸው ነው፡፡

ጥምረቱ በቅርቡ ባካሄደው የአመራር ምርጫ ላይ ዶክተር መራራ ጉዲናን በሊቀመንበርነት መምረጡ የድርጅቱን ዓላማ የበለጠ እንድጠራጠረው ያደረገኝ ሃቅ ነው፡፡ እርግጥ እንደ አንድ ዜጋ እዚያ ድርጅት አመራር ላይ ‹‹ የተቀመጠው ሰው ይሁን ጦጣ›› አይመለከተኝም ብዬ በዝምታ ባልፈው ደስ ባለኝ ነበር፡፡ በዝምታ እንዳላልፍ ያደረገኝ ግን ድርጅቱ ምን አስቦ ነው ይህን ያደረገው የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ‹‹ተመሣሣይ ላባ ያላቸው ወፎች አንድ ላይ ይበራሉ›› እንደሚባለው በስብስቡ ውስጥ ያሉት አባላት ከሞላጐደል ተመሣሣይ አቋም ያራምዳሉ ቢባል እንኳ በአንፃራዊ መልኩ ሲታዩ ከዶክተር መራራ የተሻሉ ግለሰቦች በውስጡ አይኖሩም ማለት ይከብዳል፡፡ በመሆኑም ዶክተር መራራ ገዝፈው የወጡበት ምክንያት ሌላ ሳይሆን ሥልጣን ለመያዝ ከመጋረጃ ጀርባ የተደበቀ ነገር አለ ብሎ መጠርጠር ተገቢ ነው ብዬ ስለማምን ነው፡፡

በበኩሌ ዶክተር መራራ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁርና በፖለቲካ ውስጥ ያሳለፉት ህይወትም በአንፃራዊ መልክ ሲታይ ረዘም ያለ ቢሆንም በዚህ ዘርፍ እስካሁን አንድም ለሀገር የሚጠቅም ተግባር ሲያከናውኑ አልተመለከትኩም፡፡

እንዲያውም በርካታ ድክመት ያሉባቸው ግለሰበ ናቸው፡፡ ከድክመቶቻቸውም ዋነኛዎቹ ደግሞ የጥላቻ ፖለቲካ አራማጅነታቸውና የጽንፈኛ አስተሳሰባቸው ናቸው፡፡ እርግጥ ስትራቴጂያዊ አድርባይነትንም እንደፖለቲካ ሥልት እንደሚጠቀሙ በምርጫ 97 ወቅት በተግባር ያሳዩ ፖለቲከኛ ናቸው፡፡ በጽንፈኛነት አስተሳሰብ ከተሞረደው አንደበታቸው የሚወጡት ቃላት ነገሮችን በርጋታና በጽሞና በመመርመር ችግሮችን

በውይይትና በድርድር ከመፍታት ይልቅ ፍጥጫና ንትርክን እንዲመርጡና ነገሮችን ሁሉ በጭፍን ጥላቻ እንዲመለከቱ አድርጓቸዋል፡፡

አሁንም ደግሜ፣ ደጋግሜ የማነሳው ጥያቄ መድረክ እኚህን ሰው ለምን መሪው አድርጎ መረጣቸው የሚለው ነው፡፡ እኚህን ሰው መሪ አድርጎ መምረጥ ሲታሰብ በቅድሚያ የሚታየው ጉዳይ ከአሁን በፊት በአመራርነት ያሳለፉት ተሞክሮ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ዶክተር መራራ በፖለቲካ አመራር ሰጪነት ያሳለፉት ሕይወት ጥሩ የሚባል እንዳልሆነ ሁላችንም እናውቃለን፡፡

ለምሳሌ ራሳቸው የመሠረቱትን የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ ሲመሩ በነበረበት ወቅት በአመራር ድክመታቸው የተነሳ ፓርቲው ሁለት ቦታ እንዲሰነጠቅ ጉልህ ሚና የተጫወቱ መሆኑ ሲታወቅ አሁን ሌላ ሥም ይዞ በእሳቸው አመራር ሥር የሚንቀሳቀሰው ፓርቲ ከበፊቱ እጅግ የተዳከመ ስብስብ እንደያዘ ይታወቃል፡፡

ከዚህ የበለጠ የአመራር ድክመታቸውን ገሃድ ያወጣው ሌላ እውነታም አለ፡፡ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረትን በተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበርነት ሲመሩ በነበረበት ወቅት የህብረቱ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ኦክቶበር 24 ቀን 2005 ባካሄደው አስቸኳይ ስብሰባ ከሥልጣን ያወረደባቸው ምክንያት በዕንፈኝነታቸው ነው፡፡ ዶ/ር መራራ ሕብረቱ የተቋቋመበትን የመመሥረቻ ሕግ፣ የድርጅቱን ሕግጋት እንዲሁም የህብረቱ ብሔራዊ ምክር ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ እና የህብረቱ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ኦክቶበር 6/2005 ያሣለፈውን ውሣኔ በማን አለብኝነት ጥሰው በመገኘታቸው ነበር፡፡ ታዲያ ለመመሥረቻ ሕግ፣ ለውስጥ ደንብ፣ ለጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔ እና ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ ተገዥ አይደሉም በሚል ከባድ ውንጀላ ከአሁን በፊት ከአንድ ህብረት አመራርነት የተወገዱትን ሰው ለአዲሱ ፓርቲ «መድረክ» አመራር ብቃት አላቸው

*ብሎ መምረጥ እውን ለአዲሱ ጥምረት ሕልውናና ጥቅምስ ተብሎ ነው ወይ? ፈጽሞ ሊሆን አይችልም - ሌላ የታሰበ ነገር ከሌለ በስተቀር ፡፡*

*ሌላ በፓርላማ ሕይወታቸውም ካየናቸው እኚህ ሰው ለአገርና ለህዝብ የሚጠቅም ሃሳብ ሲሰነዝሩ የሚታዩ አይደሉም፡፡ ይልቁንም የሚታወቁት ስሜት ኮርኳሪ የሆኑ ያልተመረጡ ቃላትን በመደርደር ተሳዳቢነታቸው እንዲታወቅላቸው የሚፈልጉ ጉልበተኛ እንጂ ፖለቲከኛ መስለው የቀረቡበትን ጊዜ በበኩሌ አላስታውስም፡፡ እንዲያውም በፓርላማ ወንበር ካላቸው የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ሁሉ በተለየ መልክ የሚያደርጉዋቸው ተንኳሽ ገለፃዎች ትዝብት ውስጥ ጥሏቸው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የእሳቸውን ጥያቄ ለፓርላማ ውይይት የማይመጥን በመሆኑ (መስከረም ወር 1998 ወር ላይ ፓርላማ በይፋ ሲከፈት ስነ-ሥርዓቱ በቲቪ በቀጥታ ይተላለፍ ነበር) መልስ አልሰጥም እስከማለት የደረሱበትን መግለጽ ይቻላል፡፡*

*ጥላቻ በተሞላ አነጋገራቸው የተነሳ የአንዳንድ የግል ጋዜጦች ማሻሻጫ የሆኑት ዶ/ር መራራ ለየሚዲያው የሚሰጡት ገለፃ ተመሣሣይ እና "ጠብ ያለሽ በዳቦ" አይነት እንደሆነም ይታወቃል፡፡*

*"የሕዝብ ድጋፍ ያስገኝልኛል" ብለው እስካሰቡ ድረስ ከውስጣዊ እምነታቸው ጋር የሚጋጭ ነገር እንኳን ቢሆን ለመናገር ወደኋላ የማይሉ እንደሆኑም እናውቃለን፡፡ ለምሣሌ ያህል በአንድ ወቅት በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተፈጠረውን ግጭት አስመልክቶ መንግሥት መከተል ያለበት ፖሊሲ ምን መሆን እንዳለበት በአንድ ሚዲያ ተጠይቀው ሲመልሱ ‹‹ምኒሊክ ቤተመንግሥት ውስጥ ተቀምጦ ያለው ኢህአዴግ እንደምኒሊክ ሊያስብ ይገባዋል›› ማለታቸውን አስታውሳለሁ፡፡*

*ድጋፍ ያስገኝልኛል ብለው ካሰቡ የለየለት ውሸት እንደሚናገሩም በበኩሌ ያረጋገጥኩት በተደጋጋሚ ሲሆን አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል ‹‹ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ወስጥ ጠንካራ የተማከለ መንግሥት*

የተፈጠረው በኢህአዴግ ዘመን ነው›› ማለታቸው ትዝ ይለኛል፡፡ አሁን ያለው የመድብለ - ፓርቲ ሥርዓት ሳይሆን የአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ አገዛዝ ነው ሲሉ ማድመጥም የተለመደ ነው፡፡ ብዙ የሕዝብ ልጆች ደማቸውን አፍስሰው ያመጡትን የሥርዓት ለውጥ ያጣጥላሉ፡፡

ሰሞኑን ከአንድ የግል ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ - ምልልስ ሌላ የታዘብኩትን ልንገራችሁ፡፡ ጋዜጣው የኢትዮጵያ መንግሥት የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ የሰጣቸውን መብት እንዴት ያዩታል ብሎ ይጠይቃቸዋል፡፡ መብት የሚባል ነገር ፈጽሞ አልሰጣቸውም፣ ይበልጥ ለጭቆና ነው የተጠቀመበት አሉ፡፡ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደራቸውን አልቀበልም ቢሉ እንኳ ቢያንስ ባህላቸውና ታሪካቸውን ጠብቀው እንዲኖሩ ፣ በራሳቸው ቋንቋ እንዲማሩና እንዲዳኙ መደረጋቸውን እንኳ እንደበጐ ለውጥ ሊቆጥሩት ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡

ጋዜጣው ኢህአዴግ በሥልጣን ላይ እያለ ምንም የሠራው የሚያስመሰግነው ነገር የለምን? ብሎ ለጠየቃቸው የሰጡት ምላሽ ጭራሽ ምንም ነገር የለም፣ ኢህአዴግም ጥሩ ሠርቻለሁ ብሎ ምሥጋና የሚጠብቅ አይመስለኝም ማለታቸውን አስታውሳለሁ፡፡ ጋዜጣው የትዝብት በሚመስል አጠያየቅ ለምሳሌ ትምህርትን በማስፋፋት በኩል ኢህአዴግ ጥሩ ነገር አልሰራም ነው የሚሉኝ ብሎ ሲጠይቃቸው ኢህአዴግ የሚፈልገው ቁጥር ብቻ ስለሆነ ይህም አያስመሰግነውም ነበር ያሉት፡፡ ጋዜጠኛው አሁንም ትዝብት የታከለበት ጥያቄውን ቀጥሎ የመንገድ ግንባታውንስ እንዴት ያዩታል ሲላቸው እዚያ ላይ ደግሞ ትልቁ ችግር ምን መሠለህ ሙስና ነው ይላሉ፡፡ ይህ ሁሉ የሚያመለክተው እኚህ ግለሰብ በአገርቱ ከሚካሄደው ሁለንተናዊ ለውጥ አንዱን እንኳን በበጐ ጐኑ ማየት ያልቻሉ ጨለምተኛ መሆናቸው ነው፡፡

ሌላው ደግሞ የዛሬ ሦስት አመት ገደማ ከአንድ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስም በኦሮሚያ ክልል ሕዝቡ የኦህዴድን አርማ እያቃጠለ የኦነግን አርማ በማውለብለብ ለኦነግ ድጋፉን እየገለፀ መሆኑን በአንደበታቸው ሲገልፁ በበኩሌ የተረዳሁት ሌላ ነገር ነበር፡፡ ከሁሉ በላይ የሚገርመው የጥላቻ አመለካከታቸው ከአገራቸው አልፎ በባእድ አገርና ሕዝብ ዘንድ እንዲታወቅ መፈለጋቸው ነው፡፡ እዚህ ላይ ልገልጽ የፈለግሁት በተለያዩ አገሮች ባደረጓቸው ጉብኝቶች ያደረጓቸውን ንግግሮችና በውጭ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ለሚዘጋጁ ሚዲያዎች የተናገሩትን ማለቴ አይደለም ፡፡ ለምሳሌ አንድ ወቅት ላይ በአንድ ሰው ጋባዥነት ኬንያ በሄዱበት ወቅት ‹‹ ዴይሊ ኔሽን ›› የተባለው የአገሪቱ እለታዊ ጋዜጣ አነጋግሯቸው ነበር (ጁን 5/2008)፡፡ ጊዜው በቀድሞው አምባገነን መሪ ኰሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ላይ የሞት ፍርድ ተላልፎ የነበረበት ሰሞን ነው፡፡ በዚያ ጊዜ የኬንያው ጋዜጣ የጠየቃቸው ጥያቄ ቀላል ነበር፡፡ እርስዎን ለሰባት ዓመት በእሥር ሲያሰቃይ የነበረው አገዛዝ መሪ ላይ የተበየነውን ፍርድ እንዴት ያዩታል? የሚል ነበር፡፡ ስለአገዛዙ አስከፊነት ጥቂት ነገሮችን ከጠቃቀሱ በኋላ ማሳረጊያቸው አሁን ያለውን መንግሥት ከመንግሥቱ ኃ/ማርያም ዘመን ጋር በማነፃፀር የአሁኑ አገዛዝ ከድጡ ወደ ማጡ እንደሆነባቸው በመግለጽ ነበር፡፡ እንግዲህ ከዚያ በፊት ከራሳቸው አንደበት ስንሰማው የነበረው በዚያ አስከፊ አገዛዝ ዘመን ታስረው የነበረው በሌላ ምክንያት ሳይሆን መኢሶን የተባለ የፖለቲካ ድርጅት አባል በመሆናቸው ነበር፡፡ ብዙዎቹ የዚህ ቡድን አባላት በጊዜው ሲረሸኑ እሳቸው በአጋጣሚ መትረፋቸውን ነበር የነገሩን፡፡ ያኔ የፖለቲካ ድርጅት መፍጠርም ይሁን ማሰብ የማይቻልበትን ዘመን በዚህ ዘመን ከ1987 እና 1988 ገደማ አንስተው በይፋ የፖለቲካ ድርጅት አቋቁመው አመለካከታቸውን በይፋ ከሚያራምዱበት ከዚህ ዘመን ጋር ማወዳደራቸው ሳያንስ ከዚያ የባሰ ነው ብለው በአንደበታቸው መናገራቸው የእሳቸውን ፅንፈኝነት በትክክል የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ ብቻ አልተገቱም፡፡ ለኬንያው ጋዜጣ ሳይጠየቁ የሰጡት መልስ ‹‹ ኢትዮጵያ ከኬንያ ጋር እኩል ልትሆን አትችልም፣ ምናልባት በሩጫ አሊያም በ80 ሚሊዮን ሕዝቧ ቁጥር ብቻ

*ካልሆነ›› ያሉት ጋዜጠኛውን ሊያስፈነድቀው ቢችል እንጂ ለእኛ ግን አንገታችንን ሊያስደፋ ታስቦ የተነገረ መሆኑን ነው የማምነው፡፡*

*በተለያዩ የአውሮፓና የአሜሪካ ከተሞች ሲዘዋወሩ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ባነጋገሩባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ እነዚህ ሰዎች የሚኖሩባቸው አገራት መንግሥታት ለኢትዮጵያ እርዳታ ከመስጠት እንዲታቀቡ ሲቀሰቅሱ የነበሩ መሆናቸውስ ምን ሊባል ነው?*

*ከሁሉ ሁሉ ደግሞ በቅርቡ ከቪኦኤና ዶቼዌሌ ጋር ያደረጉዋቸውን ቃለ -ምልልሶች በወጉ ያጤነ ማንም ሰው የሚረዳው ጤናማ የፖለቲካ አስተሳሰብ እንደሌላቸው ነው፡፡*

*እኚህ ሰው የደርግ መንግሥት ወድቆ አዲሱ የዴሞክራሲ ሥርዓት ከተመሠረተ በኋላ እራሳቸውን እንደ ፖለቲካ ፓርቲ አደራጅተው በይፋ መንቀሳቀስ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ በየጊዜው የሚጠቀሚት አንዲት ዓረፍተ ነገርም የእሳቸውን ማንነት በግልጽ የምታስረዳ ነች፡፡ ‹‹ የሚበላው ያጣ ሕዝብ መሪዎቹን ይበላል›› ይላሉ፡፡ አንዳንዴም ‹‹ያኔ ደግሞ እኛ አናስጥልም ›› የምትል ቅጥያ ማስከተል ይወዳሉ፡፡ ይህ አነጋገራቸው የሚጠቁመው እንዲህ ዓይነት ክፉ ቀን እንዲመጣ እጣን እያጫጬሱ የሚለማመኑ እስኪያስመስላቸው ድረስ በፓርላማ ውስጥ መናገራቸው ብቻ ሳይሆን እስካሁን ድረስ የመለሳለስ ፍንጭ አለማሳየቱ የተጠናወታቸውን ክፉ የአስተሳሰብ ደዌ አያመላክትም ትላላህትሁ?*

*ነገረ ሥራቸው ሁሉ ለስከነ የፖለቲካ አካሄድ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ለማወቅ ሌሎች በተለያዩ ጊዜያት ፓርላማ ውስጥ ያደረጓቸውን ንግግሮችና በየሚዲያው የሰጧቸውን አስተያየቶች ማጤን ተገቢ ነው፡፡*

*እንደሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች መሪዎች ስለፓርቲያቸው ከመናገር ይልቅ አብዛኛውን ጊዜ በገዥው ፓርቲ ላይ ገለፃ በማብዛት የሚጠመዱት እኚህ የፖለቲካ መሪ አቋማቸው አመጽና ብጥብጥ ወዳድ*

*(ጥል በደላላ የሚያፈላልጉ) አስመስሏቸዋል፡፡ በፖለቲካ ዓለም ውስጥ ዘላቂ ወዳጅም ይሁን ዘላቂ ጠላት እንደሌለ እርሳቸው ይጠፋቸዋል ባልልም እንደፖለቲካ ምሁርነታቸውም ይሁን እንደፖለቲከኛነታቸው ሊገነዘቡት አለመፈለጋቸው ይዘውት የተነሱት ዓላማ ምን እንደሆነ እንኳ ለማወቅ አዳጋች አድርጎታል፡፡*

*በፖለቲካ ሳይንስ ከያዙት ወረቀት ሌላ የጠለቀ እውቀት እንደሌላቸው የሚያራምዱት የጥላቻ ፖለቲካ ጥሩ ማሳያ ነው፡፡ በጥላቻ የተሞላው አንደበታቸው ከአይናቸው ይልቅ ጆሮአቸውን ለሚያምኑ የዋሆች የሚፈጥረው ተጽእኖ ቀላል እንዳልሆነ በበኩሌ አምናለሁ፡፡*

*በየአጋጣሚው ሚዲያ ፊት በቀረቡ ቁጥር አባሎቼ እየታሠሩና እየተገረፉ ነው ማለት የሚቀናቸው ዶ/ር መራራ በተለይ በፀረ- ሽብር ሕጉ ላይ ያላቸው ጥላቻ ምን ያህል የከፋ እንደሆነ በየአጋጣሚው ከመግለጽ የታቀቡበት ጊዜ የለም፡፡ ይህም ለሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ራሳቸውን ለማዘጋጀት ብዙ እንደሚቀራቸው አመላካች ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከቪኦኤ ጋር ጳጉሜ /2001 ዓ.ም. ባደረጉት ቃለ - ምልልስ ስለመጪው ዓመት ምርጫ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የሚሻለው ‹‹ እንደዝምባቡዌና ኬንያ የሥልጣን መጋራት ስምምነት ነው ›› ማለታቸውም ተለይቶ ሊጠቀስ የሚገባው ነው፡፡ ሕገ - መንግሥታዊ የሥልጣን ሽግግር ባለበት አገር ይህንን አቋም ከወዲሁ የሚያራምዱ ፖለቲከኛን የፓርቲዎች ጥምረት አመራር ማድረግ ታዲያ ለብጥብጥና ለሁከት ነጋሪት እንደመጐሰም አይቆጠርምን?*

*እርግጥ መድረክ የተባለውን የፖለቲካ ሰረገላ ለመጐተት ደፋ ቀና እያሉ ያሉትን ፓርቲዎችና ግለሰቦች ብንመለከት የቁስሉ መጠን ይለያይ ካልሆነ በስተቀር ሁሉም የየራሳቸው ችግር ስላለባቸው ስብስቡ ጥሩ መሪ ማግኘት አስቸጋሪ ሆኖበት ሊሆን ይችላል፡፡*

እዚህ ላይ መድረኮች መገንዘብ ያለባቸው እውነታ ተወደደ ተጠላም የኢትዮጵያ ህዝብ ካለፈው ስህተት ተምሮ በቀጣዩ ምርጫ የሰለጠነ የፖለቲካ ውድድር እንዲኖር መፈለጉን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ካሁን በፊት አመጽና ሰላማዊ ትግልን የመቀላቀል አባዜ ሲፀናወታቸው የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጭምር የቀድሞው አደገኛ አካሄድ እንደማይጠቅም በውል ተገንዝበው መጪውን ምርጫ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ነፃና ፍትሃዊ ለማድረግ በጋራ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በአገራችን ሕገ - መንግሥታዊ ሥርዓት ሥልጣን መያዝ የሚቻለው በምርጫ ብቻ ሆኖ እያለ በተለያዩ መንገዶች እጅን ጠምዝዞ ሥልጣን ለመያዝ የሚደረግ አንዳች ጥረት ራስን ወደ እሳት ከመወርወር ያላነሰ ተግባር እንደሆነ ይበልጥ እየተረጋገጠ መጥቷል፡፡ እንዳለፈው ጊዜ አመጽና ሁከትን ሲያራገቡ ቆይቶና ሌሎችን አሟልፎ ሠጥቶ ባለቀ ሰዓት ላይ በፓርላማ ጉያ እጠለላሁ በሚል የተሳሳተ እሳቤ ከሕግ ተጠያቂነት ለማምለጥ መሞከር ካለፈው ትምህርት ተወስዶበታልና ሁለተኛ እንደማያዋጣም ሊታወቅ ይገባዋል እያልኩ ጹሁፌን በአንድ ጥንታዊ የግሪክ ተረት ልቋጭ፡፡

አንድ ማየት የተሳነው ሰው እንስሳዎች ሲቀርቡለት ምንነታቸውን በእጁ እየዳሰሰ በመለየት ይናገር ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን የአካባቢው ሰዎች አንዲት ትንሽ የተኩላ ቡችላ ይዘው መጥተው ምንድናት ብለው ይጠይቁታል፡፡ እሱም እንደተለመደው በእጁ ቢዳብሳትም እንደወትሮው ለመለየት ቀላል አልሆነችለትም፡፡ በዚህ ጊዜ እንዲህ አላቸው ‹‹የተኩላ ልጅ ናት ወይም የቀበሮ ልጅ ናት ብዬ በእርግጠኝነት ልነግራችሁ ይከብደኛል፡፡ የምመክራችሁ ግን ይህቺን እንስሳ ከበጎች ጋር እንዳትቀላቅሏት ነው፡፡››